

# ሁሉን ችሎ
# የማለፍ ምስጢር

16-2

## አእምሮአችን፣ ፈቃዳችንና ስሜታችን ይነካል

እንደ ጳውሎስ አነጋገር ኃይልን በውስጣችን ሊያኖር የሚችለው ክርስቶስ ብቻ ነው። ኃይሉም አእምሮአችንን፣ ፈቃዳችንና ስሜታችንን መንካት አለበት። ብዙዎቻችን ኢየሱስን እንወደዋለን። ስለሆነም ከልባችን የምስጋና መዝሙር እንዘምርለታለን። ስሜታችንም ተነክቶ እናለቅሳለን። ሁኔታችንን የተመለከቱ አንዳንድ ሰዎች ለጌታ ታላቅ ፍቅር ያለን ይመስላቸዋል። እንዲሁም ስሜታችን ሲቀሰቀስ ልዩ ተስፋ ለጌታ እንገባለን። ይህ ሁሉ መልካም ይምሰል እንጂ በቂ አይደለም። ስሜታችን እንደተነካ ሁሉ ፈቃዳችንና አእምሮአችንም መነካት አለበት። በስሜት ብቻ “ብል ብል” ማለቱ ዕድሜ ስለማይኖረው ቶሎ እንደጭስ ብን ብሎ ይጠፋል። የክርቶስ ኃይል የነካው ስሜታችንን ብቻ ከሆነ፥ ሁኔታዎች በተለዋወጡ ቁጥር ጸንቶ የሚቆም ኃይል አይኖረንም። ስሜታችን በጋለ ጊዜ የገባነውን ቃል ኪዳን ስሜታችን ሲበርድ አንጠብቀውም። የክርስቶስ ኃይል በውስጣችን እንዲኖር ከፈለግን አእምሮአችንና ፈቃዳችንንም ጭምር እንዲነካ የልባችንን በር ወለል አድርገን መክፈት ይገባናል። አእምሮአችን በክርስቶስ ኃይል እንዲነካ ከፈቀድን፥ እንዲሁም የፈለገውን ነገር እንዲያደርግ ለመንፈስ ቅዱስ ነጻነት ከሰጠነው፥ በጎ ሥራውን በውስጣችን ይሠራል።

“በእግዚአብሔር እውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሳው ክርክርና ከንቱ አሳብ እናፈርሳለን፤ አዕምሮን ሁሉ እየማረክንም ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እንደርጋለን” (2ኛ ቆሮ 10፥5)። አንዳንድ ከአእምሮአችን የሚፈልቁ መጥፎ ሃሳቦችን መጣል ይገባናል። ከእግዚአብሔር ሃሳብ ይልቅ ከፍ ብለው የሚታዩት ደግሞ ዝቅ ማለት አለባቸው። በአጠቃለይ ሃሳባችን ሙሉ በሙሉ ለጌታ መታዘዝ አለበት። ይህ ካልሆነ ግን ሁለንተናችንን መቆጣጠር አይችልም። ሁሉንም ካልተቆጣጠረ ደግሞ ኃይልን ሊሰጠን አይችልም።
ኢየሱስን በጣም እንወደዋለን? ከወደድነውስ አእምሮአችንን ሁሉ እንዲቆጣጠር እንፈቅድለታለን? የሚለንን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነው? መወገድ የሚገባውን ሁሉ ከሕይወታችን ሲያስወግድ “እሺ እንዳልክ” እንላለን? እዚህ ላይ ፍቅራችን እውነተኛነቱ በሚዛን ላይ ይለካል። ብዙዎቻችን ከክርስቶስ ጋር ሙሉ በሙሉ መጠበቅ አንፈልግም። እንዲሁም በራሳችን ፈቃድና ውሳኔ መራመድን እንመርጣለን። ከክርስቶስ ጋር የቀረበ ግንኙነት ስለሌለን፥ ክፉ ሁኔታዎችን ሁሉ ታግሶ የማለፍ ኃይልና ችሎታ የለንም።
“ሁሉን በሚያስችለኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ” ለማለት የምንችለው፥ ከክርስቶስ ጋር በጣም የተቀራረበ ግንኙነት ያለን እነደሆነ ብቻ ነው። ከክርስቶስ ጋር በሚኖረን ኅብረት ደስተኞች ለመሆን ብንፈልግ፥ እሱ የፈቀደውን በሕይወታችን እንዲያደርግ የፈቀድንለት እንደሆነ ነው። ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ኅብረት ሲፈጥር፥ የአባቱን እንጂ የራሱን ፈቃድ አላስቀደመም። “እንደ አንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን” አለ (ማቴ. 26፥29)። ሁሉን በትዕግሥት ተቀብሎ ለማለፍ የሚያስቸለውን ውስጣዊ ኃይል መቀበል የሚቻለው፥ የእኛ ፈቃድ በእርሱ ፈቃድ ተለውጦ ከእርሱ ጋር የተቀራረበ ኅብረት የፈጠርን እንደሆነ ብቻ ነው።

ጳውሎስ ያጋጠመውን ችግርና መከራ መዘርዘር ብቻ ሳይሆን ለምን መከራ እንደተቀበለና መከራውን የሚታገስበትን ኃይል ከየት እንዳገኘ ይናገራል። በመከራ ላይ ያሉትን ሁሉ ማጽናናት እንድንችል እግዚአብሔር እኛን በመከራችን ሁሉ ያጽናናል። የክርስቶስን መከራ በብዛት እንደመካፈላችን መጠን እንዲሁም በክርስቶስ አማካይነት መጽናናትን በብዛት እናገኛለን (2ኛ. ቆሮ 1፥4-5)። ከእግዚአብሔር የምናገኘው መጽናናት የሚለው ሃሳብ፥ ከፍቅሩ ጋር ተመሳሳይነት አለው ማለት አይደለም። አማኝ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍቅር መለማመድ ይችላል፤ መጽናናቱን ግን ሁሉም ላይቀምሱት ይችላሉ። መጽናናት በሰው ሕይወት ትልቅ ነገር ሲሆን፥ የሚገኘውም መከራ የተለያየ ግፊትን ከቀመሰ በኋላ የሚመጣ ነው። ማጽናናት ማለት በሌላው ሰው ሕይወት ላይ ይደረሰበት አሳዛኝ ሁኔታ ማዘንና ከንፈር መምጠጥ አይደለም። ማጽናናት ከዚህ ይበልጣል። ቃሉ የመጣው ከላቲን ቋንቋ "ፎርቲካ" ከሚለው ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙ 'ኃይልና ብርታት' ማለት ነው። ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን "አጽናኝ" ብሎ ይጠራዋል (ዮሐ. 14፥16, 26)። መንፈስ ቅዱስ ላዘነው ኃይልና ብርታትን ይሰጠዋልን። "በመከራችን ሁሉ ያጽናናል" የሚለው አባባል እግዚአብሔር ኃይልና ብርታትን ይሰጠናል ማለት ነው። አጽናኙ እግዚአብሔር ወደ ሕይወታችን በመግባት በመከራ የተደቆሰውን ሕይወታችንን በማገዝ ብርታትን ይሰጠናል። "መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው፤ የዘላለም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው" (ዘዳ 33፥27)። እንግዲህ ግፊቱ ወደታች ሲጫነን ዘላለማዊ ክንዱ ከበታቻችን በመሆን ከፍ ያደርገናል። በመከራ ወደታች በተገፋን ቁጥር የበለጠ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ክንዱ ላይ ለማረፍ እየተጠጋን እንሄዳለን። ወድቀን መሬት ነካን ስንል ያኔ እጁ ላይ እናርፋለን። የእግዚአብሔርን አጽናኝነት በሕይወታችን የተለማመድን ስለምንሆን ጳውሎስ እንደ ሚለው ሌሎችን ለማጽናናት ብቁዎች እንሆናለን። ጳውሎስ "ሁሉን በሚያስችለኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ" ሲል መከራ አይሰማኝም፣ አያመኝም፣ አይቆነጥጠኝም ማለቱ አይደለም። ሥጋ ለባሽ በመሆኑ የሚያልፍበት መከራና ስቃይ ሁሉ ይሰማዋል፤ ይሁን እንጂ በውስጡ ማለፍ የሚያስችለው ልዩ ኃይልና ጸጋ ነበረው። ያም ከራሱ የመነጨ ሳይሆን ከክርስቶስ የወጣ ነበር። በውስጡ ይኖር የነበረው መንፈስ ቅዱስ በመከራው ሁሉ ያግዘው ስለነበረ፥ ኃይል እንጂ ድክመት አይሰማውም ነበር።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!**